የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

2015 ሚያዝያ ቅጽ 1 ቁጥር 9

## በዓይነቱ ልዩ የሆነ ግብርናን ማዘመንን የተመለከተ ሁነት በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ተካሔደ

የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግና ለዘመናት የአገራችንን ሕዝብ ለመመገብ ሌት ተቀን እየለፋ የኖረውን ትጉህ ገበሬ ሕይወት ለማሻሻል ታላቅ ራዕይ አንግቦ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ግብርናን ማዘመንን የተመለከተ ሁነት አካሔደ። መርሐግብሩ በፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የእርሻ ፈጠራ ክፍል ተሰናድቶ ባሳለፍነው ሐሙስ ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በኩባንያው መሰብሰቢያ አዳራሽ የተከናወነ ሲሆን በዝግጅቱም ላይ በእንግድነት የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ፣ የየክፍላቱ ቺፍ ኃላፊዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ እንዲሁም የድርጅቱ ሠራተኞች ተሳትፈዋል።




"

**በሁነቱ መጀመሪያ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ እርሻ ፈጠራ ክፍል ዳይሬክተር ወ/ሮ ሙላቷ ወልዴ ለእንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት ያስተላለፉ ሲሆን በማስቀጠልም የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ የአቅም ግንባታ (Capacity building) እና የጥናትና ምርምር ማእከል(Research and Study Center) የተሰኙ በእርሻ ፈጠራ ዘርፍ ለአገራችንም ሆነ ለመላው ጥቁር ማኅበረሰብ በዘመናዊ ግብርና የሚረጋገጥ ኢኮኖሚያዊ ልዕልናን እውን ለማድረግ ዐበይ አስተዋጽዖ ማበርከት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ይፋ ማድረጋቸው ጥናታዊ ጽሑፍ እና የኩባያውን እንቅስቃሴዎች የተመለከተ ማብራሪያ አቅርበዋል።**

በዕለቱም ታላቁ የታሪክ ምሑርና ተመራማሪ እንዲሁም የፐርፐዝብላክ የክብር አምባሳደር ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ በኢትዮጵያ የረኀብና የቸነፈር መነሻና መፍትሔዎቻቸው (The Root Cause of Famine and Drought in Ethiopia and their Solutions) እና የአፍሪካ በተለይም የኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ ግብርና (Ancient and Modern Agriculture in Africa Particularly in Ethiopia) በተሰኙ ርዕሶች ላይ ግብርናን ከማዘመን፣ የኑሮ ውድነትንም ታሪክ ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳረፍ የሚችሉ ሐሳቦችን በጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል።

በተጨማሪም በግብርና ላይ ዘርፈ ብዙ ጥናቶች እና ምርምሮች ያደረጉት ምሑር እና ሳይንቲስት ዶክተር ጸደቀ አባተ የወደፊቱ የኢትዮጵያ ግብርና (The Future Agriculture of Ethiopia) በሚል ርዕስ ግብርናችን ምን ላይ እንደሚገኝ እና መጻዒ ዕድሉ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት ጥልቅ ሙያዊ ማብራሪያ የታከለበት ትንታኔ ሰጥተዋል።

በመርሐግብሩ የጋፕ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ተባባሪ መሥራች እና የንግድ ፈጠራ ዘርፍ ባለሙያ የሆኑት አቶ መኩሪያው ተረፈ የተሞክሮ ማጋራያ እና ማነቃቂያ ንግግር አድርገዋል። አቶ መኩሪያው አክለውም ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ያነገበው ራዕይ እጅግ አስደሳችና ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ልዕልናዋ ሊመልሳት የሚችል በመሆኑ የኩባንያው ቤተሰብ ለመሆን አብረውም ለመሥራት ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በሁነቱ በተዋናይት ፍቅር ባይለየኝ ግብርናችን እና ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን ከምንም በላይ ክብር ሊሰጠው የሚሻ መሆኑን የሚያወሳ ትዕይንተ ሕዝብ የቀረበ ሲሆን በመርሐግብሩ ማጠናቀቂያ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የሰፖርት ኦፕሬሽን ቺፍ ኃላፊ ወ/ሮ እፍትታን ሶፊያ ነጋሽ የኩባንያውን ማጠቃለያ መልእክት አስተላልፈው ዝግጅቱን በማስተባበር ያሰናዱትን የእርሻ ፈጠራ ክፍል ዳይሬክተር ወ/ሮ ሙላቷ ወልዴን እንዲሁም ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡትን ምሑራን አመስግነው የእርሻ ፈጠራ ክፍል ዳይሬክተሯ ላከናወኑት ተግባር የዕውቅና ምስክር ወረቀት በኩባያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እጅ አበርክተውላቸዋል።

በመጨረሻም ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ምሥረታ ጀምሮ ለተቋሙ እድገት የተቻላቸውን ጥረት እና አስተዋጽዖ ላበረከቱት ወ/ሮ ፍሬሕይወት ገ/ሕይወት የሰፐላይ ቼይን ቺፍ ኃላፊ እና ወ/ሮ ሚሊዮን ወልዴ የሪቴይል ክፍል ዳይሬክተር እና የፐርፐዝብላክ ኢቲኤች የቦርድ አባል የዕውቅና ምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸው የመርሐግብሩ ማጠቃለያ ሆኗል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በአማራ ክልል ምእራብ ጎጃም ዞን ጃቢ ጠናን ወረዳ ጅማት ቀበሌ ያደራጀውን አንድ የኩታ ገጠም ክላስተር ማስጀመሪያ መርሐግብር አካሄደ።

ኩባንያው በአማራ ክልል ምእራብ ጎጃም ዞን ጃቢ ጠናን ወረዳ ጅማት ቀበሌ በ176 ሄክታር መሬት ላይ የሚያመርቱ 134 ገበሬዎችን በ 1 ክላስተር አደራጅቶ ወደ ሥራ ማስገባቱን የፐርፐዝብላክ ቺፍ ቴክኒካል ኦፕሬሽን ኦፊሰር አቶ አስናቀ ኃ/ሚካኤል አስታውቀዋል።
ከወራት በፊት የክላስተሩን መደራጀት ተከትሎ የግብርና ሥራዎች የተጀመሩ ሲሆን ሚያዚያ 24 ቀን 2015 የወረዳና የዞን የግብርና ሃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች በተገኙበት በይፋ ማስጀመሩ ተገልጿል።

በግብርና ስራዎቹ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በኩታገጠም የአስተራረስ ዘዴ በሚያለማቸውን የእህል ዘሮች አትክልትና ፍራፍሬ ለሃገር ውስጥ ገበያ በማድረስ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገ የሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ ተነሳሽነቱም ገበሬዎችን በክላስተሮች በማደራጀት በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች የማምረት ስራውን ከማቀላጠፍ ባሻገር አርሶአደሮችን በእውቀትና በክህሎት በማነጽ የተሻለ ገቢ አግኝተው ዘመናዊ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ ይፋ ተደርጓል።

ምስል በነብዩ ዳንኤል



“

**ዋና ኃላፊው በማስጀመሪያ መርሃግብሩ ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅትም የግብርና ግብአትና ማሽነሪዎች አቅርቦት፣ ኢንሹራንስ እንዲሁም ክምችትና የገበያ ሰንሰለት ማዕቀፉን የማመቻቸት ኃላፊነቶች በኩባንያው እንደሚከናወኑ ጠቁመው በአማራ ክልል ምእራብ ጎጃም ዞን ጃቢ ጠናን ወረዳ ጅማት ቀበሌ ይፋ የሆነው ይህ ክላስተር በክላስተር ደረጃ ለኩባንያው 4ኛ መሆኑን ገልጸዋል።**

በእርሻዎቹም ላይ በዋናነት ሌሙ የተሰኘ የበቆሎ ምርጥ ዘር በወረዳው ግብርና ክፍል አማካኝነት የቀረበ እና ከግንቦት 1 ጀምሮ ዘር የመዝራት ስራ የሚጀመር ሲሆን የተፈጥሮ ማዳበሪያን ጥቅም ላይ ለማዋል በትኩረት እየተሰራ ይገኛል።

ባሳለፍነው ሳምንት በሲዳማ ክልል ብላቴ ወረዳ የ 3 ክላስተሮች ማስጀመሪያ መርሃ ግብር መካሄዱን ያስታወሱት ሃላፊው "አርሶ አደሮች የኩባንያውን አክሲዮኖች ሲገዙ ከኢንቨስትመንቶች ትርፍ ተካፋይ ከመሆናቸው ባሻገር በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሃ ግብር የታቀዱ በርካታ የግብርና ሜካናይዜሽን ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ በመሆን ምርትና ምርታማነታቸውን ያሳድጋሉ" ብለዋል።

የፕሮጀክቱንም ውጤታማነት እውን ለማድረግ ክትትል እና ድጋፉ በሀላፊነት እንደሚቀጥል በመግለጽ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት በማሳደግ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ትልቅ መሳሪያ መሆኑን አንስተዋል።

በመጨረሻም መርሃግብሩ ከክላስተር ማስጀመሪያነት ባሻገር ለሁሉም አካላት ጥሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን አርሶ አደሮች ፐርፐዝብላክ ባቀረበላቸው የአክሲዮን ባለቤትነት ግብዣና የክላስተሮች መቋቋም ስላሳዩት ከፍተኛ ፍላጎት እና ባለድርሻ አካላት ስላሳዩት ትብብር ምስጋና

ከዚህ ጋር በተያያዘም መረጃው እስከተጠናቀረበት ጊዜ በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ ባጠቃላይ ከ6 ሚሊዮን 354 ሺህ 145 ብር በላይ በሆነ ገንዘብ የኩባንያውን ሼር በመግዛት 18,858 ገበሬዎች የፐርፐዝብላክ ባለአክሲዮን ሆነዋል።



## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ፐርፐዝብላክ ኬርስ የተሰኘ ግብረሰናይ ድርጅት ለማቋቋም በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ፈቃድ አገኘ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ ቁጥር (1) መሠረት አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በመዝገብ ቁጥር 6819 በመመዝገብ ሕጋዊ ሰውነት ማግኘቱን የኩባንያው ኮርፖሬት ሶሻል ሪስፖንሲቢሊቲ እና የፐርፐዝብላክ ኬርስ ፋውንዴሽን ዳይሬክተር አቶ ሰማኸኝ ደሳለኝ አስታወቁ።


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
AUTHORITY FOR CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS

የምዝገባ የምስክር ወረቀት

ፐርፐዝ ብላክ ኬርስ ፋውንዴሽን የተባለ አገር በቀል ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 6819 በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቶታል።

CERTIFICATE OF REGISTRATION

This is to certify that PURPOSEBLACK CARES FOUNDATION has been registered and accorded legal personality with Registry Number 6819 on April 20, 2023 as Local Organization in accordance with the Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019.

Notice: If the organization fails to discharge its responsibility to submit Activity and Audit reports, as per Proclamation No. 1113/2019, Article 70 of the proclamation "verification of existence" shall be applicable.

For more information:
Tel: +251115582422
Fax:+251115581825
P.O.Box: 14340
E-mail: info@acso.gov.et
Website: www.acso.gov.et

ድርጅቱ በዋናነት የተለያየ የንግድ ፈጠራ ሐሳብ ያላቸውን ሥራ ፈጣሪዎች አወዳድሮ የገንዘብ ሽልማት እና ድጋፍ በመስጠት የራሳቸውን ንግድ እንዲያቋቁሙ ማስቻልን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሲሆን የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አክሲዮን ማኅበር እህት ድርጅት በመሆን የሚሠራ ይሆናል ያሉት ዳይሬክተሩ የፐርፐዝብላክን የጥቁር ሕዝቦችን በኢኮኖሚ ራስን የመቻል ራዕይ እውን ለማድረግ አይነተኛ መሳሪያ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

አቶ ሰማኸኝ አክለውም ፕሮጀክቱ በ3 ዋና ዋና መንገዶች ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን እነዚህም ሥራ ፈጣሪዎችን በማወዳደር የተሻለ የንግድ ሐሳብ ላቀረቡ ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸው የገንዘብ ድጋፍ እና የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት እንዲሁም የንግድ ሥራዎቻቸውን ጨምሮ አስፈላጊ በሆነው መንገድ ሁሉ ክትትል ማድረግን ያካትታል ብለዋል።

ለፕሮጀክቱ ማስኬጃ 90 በመቶ የሚሆነው ገንዘብ ከዓለም አቀፍ ለጋሾች የሚሰበሰብ ሲሆን ቀሪው 10 በመቶ ከፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አመታዊ ትርፍ የሚገኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ከሥራ ፈጣሪዎቹ ትርፋማ የንግድ ሐሳቦች ትግበራ የሚገኘው 20 በመቶ ትርፍ ለድርጅቱ ገቢ የሚደረግ ሲሆን ድርጅቱ በሚቋቋምበት ወቅትም የውድድር፣ የስልጠናና የክትትል ማእከላትን ጨምሮ ብቁ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማብቃት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ሁሉ ያሟላ ይሆናል።

ፐርፐዝብላክ ኬርስ ፋውንዴሽን በርካታ ዜጎች በዕድሉ ተጠቃሚ ሆነው የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ ስለሚያስችል የሥራ ፈላጊዎችን ቁጥር በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚኖረው ሲሆን የንግድ ሥራ ፈጠራ ባለቤቶቹም ከተለያዩ ስልጠናዎች በኋላ በሚሰጣቸው የገንዘብ ድጋፍ የሚያቋቁሟቸው የንግድ ሥራዎች ለሌሎች ሰፊ የሥራ ዕድል እንደሚከፍቱ ይጠበቃል።

**ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ**

## ለበለጠ መረጃ

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com

**PURPOSEBLACK CARES**
**FOUNDATION**